# አርቲስት ጠለላ ከበደን ለመዘከር

ከኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች



1931 - 2014

ከዚህ ዓለም በሞት የተለየችበት የ80ኛ ቀን መታሰቢያዋ ሲከበር ለኢሕአፓ አባላት እናት፣ እህትና ጓድ የነበረችውንና እንዲሁም ኢሕአፓ እያካሄደ ባለው ሕዝባዊ ትግል ግምባር ቀደም ደጋፊ፣ ተባባሪና ተሳታፊ በመሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከተችውን ጀግናዋን አርቲስት ጠለላ ከበደን በአንክሮ እናስታውሳታለን። ከሙያዋ ጎን ለጎን ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት እንዲሁም ለሕዝቧ መብትና አንድነት በተደረጉ ትግሎች ውስጥ አኩሪ አስተዋጽኦ ያደረገችው ጠለላ ከበደ በአገራችን ታሪክ ውስጥ ጎላ ያለ ቦታ ያላት ናት።

ህዳር 12/1931 ዓ.ም ድምጻዊት ጠለላ ከበደ ለሀገራቸው ከጣልያን ወራሪ ጋር ሲዋጉ ከቆዩ በኋላ ወደ ኬንያ ተሰደው ሲኖሩ ከነበሩት አርበኛ አባትዋ አቶ ከበደ ወርቁና ከእናቷ ወ/ሮ ደስታ ብሩ ኬንያ ሲኦሎ በምትባል ከተማ ከጥበብ ተሰጥኦ እና የሰብአዊ መብት ተሟጋችነትን ተልዕኮ አዝላ ወደዚህች ምድር መጣች። እስከ 4 አመቷ በኬንያ ከቆየች በኋላ ኢትዮጵያ ነጻ በመውጣትዋ ጠለላ ከበደም ከወላጆችዋ ጋር ወደ ኢትዮጵያ ተመልሳለች

ጠለላ ከበደ በዚያን ወቅት እንደነበሩ የእድሜ እኩዮችዋ በአዲስ አበባ ውስጥ ሰፈሯ አካባቢ በሚገኝ የቄስ ት/ቤት ከየኔታ እግር ስር ቁጭ ብላ ፊደል ቆጥራለች:: በኋላ ዲታ ዲባ የሚባሉ ጣልያናዊ ት/ቤት፤ ከዚያም ጊዮርጊስ ት/ቤት፤ ሃኪም ወርቅነህ የሚባል የማዘጋጃ ት/ቤት፤ በመጨረሻም ሚሲዮን ላዛሪስት የአሁኑ ሴንትሜሪ ት/ቤት ተብሎ በሚታወቀው ት/ቤት እስከ አምስተኛ ክፍል ተምራለች።

የዘፋኝነት ተሰጥኦ የነበራት ጠለላ ከበደ በቀዳማዊ ኃ /ሥላሴ ያሁኑ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ትያትርን በ1948 ዓ/ም ገና ታዳጊ ወጣት ሳለች በመሪ ድምጻዊነት ተቀላቅላለች:: በተዋናይነት፤ በተዋዛዥነት በድምጻዊነትም ያገለገለች ሁለገቧ ድምጻ መረዋዋ አርቲስት ጠለላ ከበደ በተለያዩ ቴያትሮች ውድቅት ፣ ሀሁ በስድት ወር፣ ቴዎድሮስን ጨምሮ ከ30 በላይ ቴያትሮች ላይ ተሳትፋለች:: ጠለላ ከበደ ልዩ ልዩ ትዕይንት ጥበባት ዝግጅት፣ዘመኑ በሚፈልገው በተለያዩ የቅስቀሳ የኪነጥበ ስራዎች ላይ በመሳተፍ በየክፍለሀገሩ በመዞር የኪነጥበብ እድገት ከአዲስ አበባ ውጪ ያለው ማህበረሰብ እንዲቋደስ የበኩሏን ጥረት ለማድረግ ያልተበገረች እንስት መሆኗን የስራ ታሪኳ ያስረዳል፡

አርቲስቷ ለ32 አመት በኢትዮጵያ ብሄራዊ ቴአትር ካገለገለች በኋላ መስከረም 1/1983 ዓ/ም ጀምሮ በጡረታ ብትገለልም በሌላው የህይወቷ ገጽ ለህዝብ ኖራለች::

ጠለላ ከበደ ከወጣትነቷ ጊዜ ጀምሮ በነበራት ከፍተኛ የሀገርና የህዝብ ፍቅር ከሙያዋ ባሻገር ለዴሞክራሲ ፍትህና እኩልነት ስትታገል ቆይታለች። በአካባቢዋ፤ በሙያ ባልደረቦቿ በጣም ተወዳጅ የነበረችው ጠለላ ከበደ ለቆመችለት አላማ ወደኋላ የማትል፤ ፍትህ ሲጓደል ድምጿን ለማሰማት የማታፈገፍግ፤ አድርባይነትን በጣም የምትጠየፍና አካፋን አካፋ እያለች በቃሏ የኖረች የግንባር ስጋና እውነተኛ የህዝብ ልጅ ነበረች::

"ሎሚ ተራ ተራ" የሚለውን ዘፈን ዘፈንሽ በመባል ጠለላ ከበደና ከሷ ጋር ሌላ ስድስት የሙዚቃ ባለሙያዎች በ1967 ዓ.ም በደርግ ካድሬዎች ለአራት ወር ከስድስት ቀን ለእስር ተዳርገዋል። ጦር ፍርድ ቤት ቀርበው በዋስ ከተፈቱ በኋላም ጠለላ ከበደ ለሁለት አመት ያህል ከአዲስ አበባ አካባቢ እንዳትንቀሳቀስ፤ ከናዝሬት አልፋ እንዳትሄድ፤ በግዞት እንድትቆይ ተፈርዶባታል።
በመስከረም 10/1987 ዓ.ም ፕሮፌሰር አስራት በወያኔ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ ፍትህን ለመጠየቅና ድምፃቸውን ለማሰማት በፍርድ ቤቱ አካባቢ ከነበሩት ለእስር ከተዳረጉት 1500 ሰዎች መካከል አንዷ ጠለላ ከበደ ነበረች። በዚያን ቀን እየተደበደቡ ሰንዳፋ ተወስደው ፀጉራቸው ተላጭቶ ታስረዋል። 1000 ሰዎች ይቅርታ እንዲጠይቁ ተደርገው ሲለቀቁ ጠለላ ከበደ ከሌላ 500 ሰዎች ጋር ይቅርታ አንጠይቅም በማለታቸው ለተጨማሪ 25 ቀናት ታስረው በከፍተኛ የህዝብ ግፊትና የውጭ ጣልቃ ገብነት ለመፈታት በቅተዋል። ከእስር ከተፈታች ከሶስት ወር በኋላ አማራጭ ሃይልና መላው አማራ መስቀል አደባባይ በጠራው ሰልፍ ላይም ከፍተኛ ተሳትፎ አድርጋለች። በስደት ሰሜን አሜሪካ ከመጣች ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ የ ኢሕአፓ ጠንካራ ደጋፊ በመሆን ለረጅም አመታት ስታገለግል እንደነበር ታሪኳ ያስረዳል።

አርቲስት ጠለላ ከበደ በጎ አድራጊ ድርጅቶች ችግረኞችን በመርዳት በሚያደርጉት የገቢ ማስገኛ ድርጅት ገቢ ማስገኛ ዝግጅት እንድትሳተፍ ስትጠየቅ ጥሪውን በመቀበል በሞያዋም ሆነ በገንዘብ አስተዋጽኦ በማድረግ ሰብአዊ አገልግሎት ሰጥታለች::
ጠለላ ከበደ 10 ልጆች 18 የልጅ ልጆች 3 የልጅ ልጅ ልጅ ያፈራች እናት ነበረች።
ድምጻዊት ጠለላ ከበደ በአደረባት ህመም ለጥቂት ቀናት በህክምና ስትረዳ ቆይታ በተወለደች በ83 ዓመቷ በስደት ትኖርበት በነበረው ሰሜን አሜሪካ ሜሪላንድ ግዛት በተወለደችበት ቀን ህዳር 12/2014 ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታለች። አስከሬኑም ወደ ኢትዮጵያ ሄዶ ለረጅም ዓመታት በኪነጥበብ ዘርፍ ባገለገለችበት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር የአስከሬን ስንብት ከተደረገ በኋላ በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በክብር አርፏል።


አርቲስት ጠለላ ከበደ የኢሕአፓ ጠንካራ ደጋፊ በመሆን ለትግሉ አስተዋጽኦ ማድረግ የጀመረችው ወደ አሜሪካ ከመጣች በኋላ ነው። በ1986 ዓ.ም. ለሰላም እና ለእርቅ ወደ አገር ቤት ገብተው በወያኔ አገዛዝ ታስረው የነበሩ የኢሕአፓ አባላትን እነ ጓዲት ገነት ግርማን እና ሌሎችን እስረኞችን ወህኒ ቤት ድረስ ተመላልሳ በመሄድ ጠይቃለች። ከእስር ከተለቀቁም በኋላ በትግላቸው እንዲቀጥሉ አበረታታለች። ከኢሕአፓ ጋር የቀረበ ግንኙነት የፈጠረችው ግን ወደ አሜሪካ ከመጣች በኋላ ነው።

ጠለላ ከበደ ወደ አሜሪካ ከመጣች በኋላ ከኢሕአፓ አባላት ጋር ልትቀራረብ የቻለችው የዓለም አቀፍ የሴቶች ድርጅት (ኢሴአድ) በተባለው ድርጅት ውስጥ ተሳታፊ በሆነችበት ወቅት ነው። የሴቶችን መብት ለማስከበር መሠረታዊ ዓላማው አድርጎ የተመሰረተው የዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ የሴቶች ድርጅት ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ በነበረበት ወቅት አርቲስት ጠለላ ከበደ ተሳታፊ ነበረች።







ጠለላ ከበደ ከፍተኛ የአገር ፍቅርና ስሜት ነበራት። በወቅቱ ሥልጣን ላይ የነበረው የወያኔ ቡድን አቅዶ በተግባር ያዋለው ዘረኛና ከፋፋይ ፖሊሲ እና እንዲሁም በሕዝብ ላይ ሲያካሄዳቸው የነበሩት አሰቃቂ አፈናዎችና ጭፍጨፋዎች ከልብ ያሳዝኗትና ያስጨንቋት ነበር። በመሆኑም የሕዝብ መብትና ክብር ሊጠበቅ የሚችለው ሆነ የአገር ሉዓላዊነት የሚከበረው የወያኔው ቡድን ከሥልጣን ሲወገድ መሆኑን ከልብ አምናና ተቀብላ ኢሕአፓ በሚያካሄደው ሕዝባዊ ትግል ውስጥ ለመሳተፍ ወሰነች። ከ2001 ጀምሮ የዋሽንግተን ዲሲ እና አካባቢው የኢሕአፓ ደጋፊዎች ስብስብ አባል ሆና እስከ ዕለተ ሞቷ ድረስ ለትግሉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክታለች። ትግሉ እንዲጠናከር ሀሳብ በማመንጨት ሆነ ምክር በመስጠት ካበረከተችው አስተዋጽኦ በተጨማሪ በገንዘቧና በጉልበቷ ያልተቆጠበና ያልተቋረጠ እርዳታና እገዛ አድርጋለች። በተለያዩ ሕዝባዊ መድረኮች ላይ ስታቀርባቸው ከነበሩት ጠቃሚ ሀሳቦች በተጨማሪ የወያኔን አገዛዝ ለመቃወም በተዘጋጁ የተቃውሞ ሰልፎች ሁሉ የዕድሜ መግፋት ሳይበግራትና ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል በግምባር ቀደምትነት ተሳትፋለች።








የአርቲስት ጠለላ ከበደ ተሳትፎ ሁለ ገብ ነበር። በአካል ተገኝቶ መሥራት በሚያስፈልገበት ቦታ ላይ ጉልበቷን ሳትቆጥብ በመሳተፍ፣ የገንዘብ አስተዋጽኦ በሚያስፈልገው ሥራ ላይ የራሷን ገንዘብ በመለገስና ሌሎች አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ በመገፋፋት፣ ለትግል አጋሮቿ ምክር በመስጠትና ተመክሮ በማስተላለፍ፣ እንዲሁም በሙያዋ ጣዕመ ዜማዋዎችን በማሰማት ታጋዮችን ስታበረታታ ቆይታለች። የኢሕአፓ ምሥረታን ለማስታወስ በዋሽንግተን ዲሲ በተዘጋጁ በዓሎች፣ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ምሽቶች፣ እና ሕዝባዊ መድረኮች ግምባር ቀደም አደራጅና ተሳታፊ የነበረች ሲሆን በአሜሪካ የተለያዩ ከተሞችም በስፖርት ፌዴሬሽን በተዘጋጁ በዓሎች ላይ በመገኘት አስተዋጾ አድርጋለች።











ከላይ በ 39ኛው የኢሕአፓ ምሥረታ በዓል ላይ ያቀረበችውን ጣዕመ ዜማ የሚቀጥለውን ማስፈንጠሪያ (link) ተጭኖ ማዳመጥ ይቻላል።

https://youtu.be/jLQhigD69a8

ጠለላ ከበደ የዕድሜያዋ መግፋትም ሆነ መጨመር ተሳትፏዋን አላደከመውም። ደከመኝ ሰለቸኝን የማታውቀው ውድ እናታችን፣ እህታችንና የትግል አጋራችን ፓርቲው በዋሽንግተን ዲሲም ሆነ በሌሎች የአሜሪካ ግዛቶች በሚያደርገው እንቅስቅሴ ሁሉ ተሳታፊ በመሆን እስከ ዕለተ ሞቷ ድረስ አገልግሎቷን ስታበረክት ቆይታለች።

የኢሕአፓ አመራር ኮሚቴ የጠለላ ከበደን ከፍተኛ አስተዋጽኦ በመረዳት በህዳር 2008 ዓ.ም. የአገር ወዳድ የምስክርነት ሽልማት አበርክቶላታል።



የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ

አገር ውዳድና ታጋይ የሆኑት

**ወይዘሮ ጠለላ ከበደ**

*ኢሕአፓ እያካሄደ ያለውን ሕዝባዊ ትግል ለማጠናከር ላበረከቱት የጎላ ሁለገብ አስተዋጽኦ ድርጅቱ ኢድናቆቱን በመግለጽ ይህንን የምስክር ወረቀት አበርክቶላቸዋል።*

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ

ታዋቂዋ፣ ተወዳጇና ታጋይዋ አርቲስት ጠለላ ከበደ በህይወት ዘመኗ ብዙ ውጣ ውረዶችን አሳልፋለች። በግል ጽፋ ያስቀመጠችውም ሆነ እሷን ከልጅነቷ ጀምሮ የሚያውቋት ወዳጆቿ በመጽሐፍ ወይም በሌላ መልክ ጽፈው ያሰራጩት ታሪክ ባይኖራትም በ2001 ዓ.ም. ለደብተራው ድረ ገጽ የሰጠችው ቃለ ምልልስ በዕድሜ ዘመኗ ያለፈችበትን ውጣ ውረዶችና ገጠመኞች ግልጽ ያደርጋል።

ከደብተራው ድረ ገጽ ጋር ያደረገችውን ቃል ምልልስ በሚቀጥለው ማስፈንጠሪያ (link) ማየት ይቻላል

https://youtu.be/wF2Zqn2KxnYhttps://youtu.be/wF2Zqn2KxnY

እጅግ የምንወዳት ጠለላ ከበደ በተወለደችበት ቀን ኅዳር 12 2014 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ስትለየን የተሰማን ሀዘንና ድንጋጤ ከፍተኛ ነበር። ሙሉ ጤነነት የነበራትና እኛ ካወቅናት ጀምሮ ሀኪም ቤት ገብታ የማታውቀው የትግል አጋራችን በአንድ ሳምንት ሕመም በድንገት ስትለየን ለማመን አስቸግሮን ነበር። ሀዘኑ ከባድ ቢሆንም በከፍተኛ የሀገር አፍቃሪነቷ የትግል ተባባሪያችን በመሆን ያደረገችውን አስተዋጽኦ እያደነቅን እንዘከራታለን። ተወዳጇ ጠለላ ከበደ ሕይወቷ ያለፈው ዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ ቢሆንም አስከሬኑ ወደ አዲስ አበባ ሄዶ የቀብሯ ሥነ ሥርዓት በቅድስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን ከምትወደው ልጇ ከወጣት ቢኒያም ዩሐንስ ገ/ማርያም ጎን በክብር ተፈጽሟል።



ለቤተሰቦቿ፣ ለወዳጆቿ እና ለትግል አጋሮቿ መጽናናትን እንመኛለን።

ነፍስ ይማር !